DMU

**Journal of Interdisciplinary Studies 7(2023) 1010-1024**

Journal homepage: www.jims.dmu.edu.et

DMU-JIDS

**Volume 7(2), Dec 2023**

# የሐይማኖት መቻቻል እሴቶች፣ በደቡብ ወሎ ዞን ቦረና ወረዳ ማሳያነት

*ሙሐመድ ሰኢድ ሙዙ[1,*]*

[1]የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል፤ መቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲ፤መቅደላ አምባ፤ ኢትዮጵያ

*Corresponding Author's Email: muzuseid2011@gmail.com

## *አጠቃሎ*

*የጥናቱ ዋና ዓላማ በደቡብ ወሎ ዞን ቦረና ወረዳ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በአብሮነት ለመኖር ያስቻሏቸው የመቻቻል መገለጫ እሴቶችን ማስተዋወቅ ነው። ጥናቱ አይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በገለጻ ስልት ተካሂዷል። በጥናቱ ማህበረሰቡ ውስጥ የሚታዩ ፎክሎራዊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አገልግሎት ላይ የዋሉት መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ምልከታና ቃለመጠይቅ ናቸው። መረጃዎቹ የተሰበሰቡት እሴቶቹ በሚገኙበት ባህላዊና ማህበራዊ ዓውድ ውስጥ ነው። ለዚህም አጥኚው ለስምንት ወራት ያህል መረጃዎችን ተመልክቷል። በታላሚ ንሞና ዘዴ የተመረጡ ስምንት ሰዎችም በቃለመጠይቅ በመረጃ አቀባይነት ተሳትፈዋል። በጥናቱ አገልግሎት ላይ የዋለው የጠቀሜታዊነት ፎክሎራዊ ንድፈ ሀሳብ ሲሆን አይነታዊ የምርምር ንድፍን ተከትሎ በገላጭ የምርምር ስልት ተካሂዷል። በደቡብ ወሎ ዞን ቦረና ወረዳ ለአብሮነት አስተዋጽዎ ያላቸው የመቻቻል እሴቶች በርካታ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ በሁለት ፎክሎር ዘውጎች (ሀገረሰባዊ ልማድ፣ ማህበረፖለቲካዊ ተቋም) ስር ሊጠቃለሉ የሚችሉ ናቸው። ይሄውም ሀገረሰባዊ መድሀኒት፣ ሀገረሰባዊ እምነትና ሀገረሰባዊ ጋብቻ በሀገረሰባዊ ልማድ ስር ይካተታሉ። እድር፣ ሀገረሰባዊ ዳኝነትና ጅጌ/አዝማች ደግሞ በማህበረፖለቲካዊ ተቋም ስር ይመደባሉ። መረጃዎቹን በማደራጀትና በመተንተን በተገኘው ውጤት መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴቶች ለቦረና ማህበረሰብ የአብሮነት፣ የእርስ በርስ ትስስር ማለት ነው። በቦረና ማህበረሰብ የጤና እክል የገጠመው ወይም አጋንንት የለከፈው ክርስቲያኑም ሆነ ሙስሊሙ በልቡ አምኖ ጤንነቱን ለማግኘት ወደነዚህ የፀበል ቦታዎች ይሄዳል። ከጸበላቸው አልፎ እምነታቸውን ይቀበላል፤ በመስቀሎቻቸው ይታሻል። ማህበረሰቡ በአካባቢው የሚከሰቱ የበረዶና የዝናብ መብዛት ችግሮችን ለመቅረፍ ሀገረሰባዊ እምነቶችን ይተገብራል። ከጋብቻ አንጻርም የክርስትና ወይም የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ መሆን የጋብቻ መስፈርት አይሆንም። የሙስሊም ልጅ የክርስቲያን ልጅ፡ የክርስቲያን ልጅ የሙስሊም ልጅ ታገባለች፤ ያገባል። ሽማግሌዎች በአዋቂነታቸው፣ በታማኝነታቸው፣ በትዕግስታቸው፣ በማህበራዊ ደረጃቸውና በኢኮኖሚ አቅማቸው መሰረት ይመረጣሉ። ሽማግሌዎቹን ለመምረጥ እስላም ወይም ክርስቲያን መሆን በመስፈርትነት አይወሰድም፤ እስላምም ክርስቲያንም ሊመረጥ ይችላል፤ ክርስቲያኑም ሙስሊሙም ለብቻው ቀሬ ወይም እድር የለውም፤ ሁለቱም በአንድ ቀሬ ውስጥ ይሳተፋሉ። ክርስቲያኑ፤ ሙስሊሙ ልጁን ሲድር፣ ሙስሊሙም ክርስቲያኑ ሲድር አዝማች ይዞ ከባለጉዳዩ ጋር ለሙስሊም ወይም ለክርስቲያን እንግዶች ድግስ ያዘጋጃል። ይህም በማህበረሰቡ ዘንድ ያለምንም የሀይማኖት ልዩነት ማህበረሰቡ ተቻችሎ በአብሮነት እንዲኖር አስችሎት ቆይቷል።*

**ቁልፍ ቃላት፤** *ሀገረሰባዊ ልማድ፣ ማህበረፖለቲካዊ ተቋማት*

# Values of Religious Tolerance, in Borena District; South Wollo Zone

*Muhammed Seid Muzu*[1,*]

[1]Department of Ethiopian Language and Litratute Amharic, College of Humanities and Social Science, Mekdela Amba University, Mekdela Amba, Ethiopia

*Corresponding Author's Email Email; muzuseid2011@gmail.com

**Abstract**

*The general objective of the study is to introduce the Values of Religious Tolerance that enable the followers of Christianity and Islam to live together in Borena district of South Wollo zone. The study was conducted using descriptive method of qualitative research design. The study has used observation and interview as a data collection tool to collect folklore Values of Religious Tolerance in the community. The data were collected in the real culture and social context of the studied society for eight months consequently by the researcher. Eight people selected through the purposeful sampling method participated in the interview as data receivers. The research has used functional folkloric theory to investigate the importance of religious values of tolerance in the society. The values used for the study are the folklore aspects that the society practices and has in its daily life. According to the results of the study, there are many folkloric values of religious tolerance that contribute to solidarity in South Wollo Zone Borena District. And the main ones can be summarized under two folklore genres (Social custom, socio-political institution). i.e folk-medicine, folk-belief, Cultural marriage are under Social custom. And Edir, traditional judiciary and Jige/Azmach are under Socio-political Institution. According to the results obtained by organizing and analyzing the data; for Borena district society, values of religious tolerance mean togetherness, social cohesion. In Borena; the Christian or the Muslim believes in his/her heart and goes to these places of wholly water (`Tsebel`) to get relief from their health and devil sprits. S/he will be healed by their crosses. Moreover, the community applies traditional beliefs to overcome the problems of storm and snow in the area. In terms of marriage, being a follower of Christianity or Islam is not a requirement in their marriage culture. A Muslim girl/boy can marries a Christian boy/girl, or vice versa. The traditional judges (elders 'Shimagles') were chosen based on their wisdom, loyalty, patience, social status and economic potential. Being Muslim or Christian is not considered as a requirement for electing the elders and Edir leaders. Moreover, when a Christian marries his/her daughter/ boy, a Muslim can participate and share food coast of weeding program food ceremony traditionally; i.e Azmach. This food ceremony, Azmach may be prepared for Muslims or Christians. It is fixed in communicating with the bride's family. Generally, folk-medicine, folk-belief, Cultural marriage, Edir, traditional judiciary and Jige/Azmach made the Borena society to live in harmony without any religious differences.*

**Keywords**: *Social Custom, socio-political institutions*

## 1. መግቢያ

በኢትዮጵያ የተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮች የመቻቻል እሴት ፈጥረው ለዘመናት መኖራቸውን ምሁራን ይገልጻሉ (አብዱላህ 2012፣ አቢንክ 1998፣ ብራውካምፐር 1992)። ኢትዮጵያ የብዙ ባህሎች መገኛ ሀገር ነች። ባህለ-ብዙነት ከሚገለፅባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ በአንድ ሀገር ውስጥ የተለያዩ ሃይማኖቶች አብረው መኖራቸው ነው። የዚህ ጥናት ትኩረት በደቡብ ወሎ ዞን ቦረና ወረዳ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ማህበረሰብ መካከል ያለውን የመቻቻል እሴት ከፎክሎር ዕይታ አንፃር ማጥናት ነው።

የመቻቻል ርዕሰ ጉዳይ በኢትዮጵያ ከቤተ-መንግስት እስከ ቤተ-እምነት፤ ከልሂቃኑ እስከ ብዙሃኑ የጋራ ርዕሰ ጉዳይ በመሆን በተደጋጋሚ ሲነገር ይሰማል። ነገርግን እነዚህ አካላት የመቻቻል ጽንሰሀሳብን የሚገልጹት ጽንሰሃሳቡን እንደተረዱበት መንገድ፣ እንደ እይታቸውና እምነታቸው ወይም እንደየግል ፍላጎታቸውና እንደየአጀንዳቸው ነው (ጌታዋ፣ 2008)።

መቻቻል በኢትዮጵያ ምንም እንኳ የብዙሃን አጀንዳና በየዕለቱ ተደጋግሞ ሲነገር የሚደመጥ ርዕሰ ጉዳይ ቢሆንም ብዙሀኑን የሚያግባባና የሚያስማማ ጽንሰሃሳብ አይደለም። መቻቻል የሚለው ጽንሰሃሳብ አንድምታው በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ነው። ለምሳሌ መቻቻል በጥሬ ትርጉሙ "ጥሩ ነገር አይደለም ግን ቻለው! ዋጠው! ወይም ታግሰህ አሳልፈው! አለያም ሆድ ከአገር ይሰፋል እንደሚባለው ነገሩን ለፈጣሪ ሰጥተህ ተወው! ወዘተ" እንደማለት ነው። በዚህ አሉታዊ ፍቺ መሰረት መቻቻል የሚለው ጽንሰሃሳብ ታጋሹ ትዕግስቱ እያለቀ ሲሄድ "በቃ! እስካሁን ድረስ ታግሻለሁ! ትዕግስትም ልክ አለው! እስከ መቼ ድረስ እታገሰዋለሁ! እችለዋለሁ! እለማመጠዋለሁ! ወዘተ" ብሎ ወደግጭት ሊያመራ ወይም የግጭት መንስኤ ሊሆን እንደሚችል የሚጠቁም አንድምታ አለው (ጌታዋ፣ 2008)።

የመቻቻል ጽንሰሃሳብ አወንታዊ አንድምታም አለው። "መቻቻል" የሚለውን የአማርኛ ቃል ደስታ ተክለወልድ፤ አዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት (1962) መሸካከም፣ መወሳሰን፣ መጣወር" ሲል ይፈታዋል። በዚህ መሰረት መቻቻል ማለት መረዳዳት፣ መደጋገፍ፣ መተጋገዝ፣ መተሳሰብ፣ መተዛዘን፣ ከእኔ ይልቅ ላንተ (አንተ-ትብስ፣ አንቺ ትብሺ) መባባል ወዘተ የሚሉትን ጽንሰሃሳቦች ያዘለ ትርጉም አለው። ሃይማኖታዊ መቻቻል በተለያየ የሃይማኖቶች ተከታይ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል የሚፈጠር የመቻቻል አንዱ ገጽታ ነው።

ይህ ጥናት የተካሄደበት ቦረና ማህበረሰብ ከሚታወቅባቸው ባህሎች መካከል አንዱ መቻቻል ነው። በማህበረሰቡ ትርጓሜ መሰረት መቻቻል "አብሮ፣ የሚያለያዩ ነገሮችን ወደጎን በመተው አንድ ሆኖ መኖር" ማለት ነው። ይህ የመቻቻል ባህል በአካባቢው በልዩ ልዩ ባህላዊ እሴቶች ይገለጻል (ቀሲስ ፍቅረማሪያም፣ ቃለመጠይቅ መጋቢት 16/2016)።
ፎክሎር የሚለው ቃል ፎክ (folk) እና ሎር (lore) ከሚሉ ሁለት የእንግሊዘኛ ቃላት ተጣምሮ የተገኘ ሲሆን ፎክ (folk) ማለት ህዝብ፣ ማህበረሰብ፣ ቡድን ወይም ክፍል ማለት ነው። ሎር (lore) ማለት ደግሞ ህዝቦች በጋራ የሚጠቀሟቸው የጋራ እውቀቶች (ጥበቦች) ማለት ነው። በአጠቃላይ ፎክሎር የህዝብ እውቀት ማለት ነው ተብሎ ሊበየን ይችላል (ፈቃደ 1991፣ ሠሎሞን 2007)።

የፎክሎር ምንነትና ምድቦችን በሚመለከት ወጥና ሁሉን የሚያስማማ ብያኔና አከፋፈል ያለ አይመስልም (ፈቃደ 1991፣ ሠሎሞን 2007)። እንደ ፈቃደ (1991) ገለጻ ፎክሎር የሰዎች መንፈሳዊና

ቁሳዊ ባህል ሲሆን እርስ በርሳቸው የማይፈታ ዝምድና ባላቸው አራት አብይ ዘውጎች ይከፈላል፡፡ እነሱም ስነቃል፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሀገረሰባዊ ልማድና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ናቸው፡፡ ሠሎሞን (2007) በበኩሉ ፎክሎር በውስጡ በርካታ ጉዳዮችን እንደሚያካትትና በአራት ምድብ ማጠቃለል እንደሚከብድ በማስረዳት በስድስት ዘውጎች (ስነቃል፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሀገረሰባዊ ልማድ፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፣ ሀገረሰባዊ ውክልናና ማህበረፖለቲካዊ ተቋም) ከፍሏቸዋል፡፡ ይህ ጥናትም የሠሎሞን (2007) የፎክሎር ዘርፍ አመዳደብን መሰረት አድርጎ ተካሂዷል፡፡ ሃይማኖታዊ መቻቻል በአንድ አካባቢ በጉርብትና በሚኖሩ በተለያየ የሃይማኖት ተከታይ ግለሰቦችና ቡድኖች መካከል የሚፈጠር የመቻቻል አንዱ ገጽታ ሲሆን የፎክሎር አንዱ አብይ ዘርፍ በሆነው በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ ይጠናል፡፡

የተለያዩ ሃይማኖቶች ያሏቸው የአንድ ሀገር ህዝቦች በልዩነቶች ምክንያት ወደ ግጭት እንዳይገቡ ለመከላከል ከሚረዱ መፍትሄዎች አንዱ የመቻቻል እሴቶችን በጥልቀት ማጥናትና ማስተዋወቅ ነው (ቶኒ፣July 2013)፡፡ ይህን እውን ለማድረግም የሃይማኖት መቻቻል ፅንሰ-ሀሳብ በየእለቱ በሚደረጉ ባህላዊ ክዋኔዎች አማካይነት ልዩነትን አክብሮ አንድነት እንዴት ጎልቶ እንደሚወጣ በማጥናት ማስተዋወቅ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ጥናትም ተጠኚው ማህበረሰብ የፈጠራቸው፣ ያዳበራቸው የሃይማኖት መቻቻል መገለጫ የሆኑ ባህላዊ እሴቶችን በመለየት ለማስተዋወቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ በሃይማኖት ልዩነት ያላቸው ማህበረሰቦች በአብሮነት መኖራቸውን የሚያሳዩ እሴቶች ላይ ብቻ ያተኩራል፡፡

## 2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በአብሮነት ለመኖር ያስቻሏቸው የመቻቻል መገለጫ እሴቶችን በመለየት ማስተዋወቅ ነው፡፡ ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎችም አሉት፡፡

- የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በአብሮነት ለመኖር ያስቻሏቸው የመቻቻል መገለጫ ሀገረሰባዊ ልማዶችን መለየት፣
- የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በአብሮነት ለመኖር ያስቻሏቸው የመቻቻል መገለጫ ማህበረፖለቲካዊ ተቋማትን መግለጽ፣
- ሀገረሰባዊ ልማዶች እና ማህበረፖለቲካዊ ተቋማቱ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በአብሮነት (በመቻቻል) ለመኖር ያስቻሉበትን መንገድ መግለጽ ናቸው፡፡

## 3. የጽንሰሀሳብ መነሻና የጥናቱ ዘዴ

### 3.1 የመቻቻል ጽንሰሀሳብ

መቻቻል ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ቡድኖች መካከል የሚፈጠር የእርስ በእርስ መስተጋብር ሲሆን በውስጡ የሚያካትታቸው አራት ደረጃዎች አሉ፡፡ እነዚህ ደረጃዎችም ልዩ ልዩ አመለካከቶችንና እምነቶች መኖራቸውን ማወቅ፣ ማክበር፣ ማድነቅ እና መኖራቸውን አውቆ መቀበል ናቸው (ሩቂያ፣ 2018)፡፡
እንደ ሩቂያ (2018) ገለጻ በዓለም ላይ ያሉ ማህበረሰቦች ሁሉ መኖራቸው እንዲታወቅ፣ ባሉበት ደረጃ መከበር፣ ከተቻለ ደግሞ በአኗኗራቸው መደነቅን ይፈልጋሉ፡፡ በመጨረሻ ደረጃ መኖራቸውን ታውቆ ተቀባይነትን ማግኘት ይሻሉ፡፡

መቻቻል የሚለው ጽንሰሃሳብ አሉታዊ አንድምታ ያለውን ያህል አወንታዊ ፍች አለው፡፡ እንደ ዩኒስኮ የመቻቻል ብያኔ “መቻቻል የሞራል ግዴታ ብቻ ሳይሆን ፖለቲካዊና ህጋዊ ቅድመ ሁኔታ ጭምር ነው፡፡ ለሠላም መስፈን አስፈላጊ ምግባር የሆነው መቻቻል ግጭትን በሰላም እሴት

ለመቀየር የራሱን አስተዋጽዎ ያደርጋል። እንደ ዩኒስኮ ገለጻ መቻቻል፤ ሽንፈት፣ ውርደት ወይም ጥቅምን አሳልፎ መስጠት አይደለም። መቻቻል ዓለምአቀፍ ሰብዓዊ መብቶችንና የሌሎችን መሠረታዊ ነጻነቶች እውቅና ከመስጠት የሚመነጭ አዎንታዊ አመለካከት ነው (UNESCO፣ 1995)።

እንደ ሙርፊ (1997) ገለጻ፣ መቻቻል በአንድ ሰው ፈቃደኝነት የተለያዩና ተቃራኒ የሆኑ ሀሳቦችን የመቀበል፣ የአንድ ግለሰብ/ቡድን እምነት (አመለካከት) እውነተኛ መሆን አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ፍርድ ከመስጠት መቆጠብ ነው። መቻቻል የአንዱ ወገን እምነት እውነትነት የሌለው ውሸት ወይም በተቃራኒው ነው ብሎ ገለጻ ከመስጠት የተቆጠበ ነው።

የመቻቻል ፅንሰሀሳብ ከመልካም አተያይ ጋር የተቆራኘ የማህበራዊ ግንኙነት መስተጋብር ነው። መቻቻል ከግለሰብ እስከ ቡድን እንዲሁም ከሀገር እስከ መንግስታት የሚገለፅ ሰፊ ጽንሰሀሳብ ነው። በመሆኑም መቻቻልን በፅንሰሀሳብ ደረጃ እንዲህ ነው ብሎ ከመተንተን ይልቅ በቡድኖች መካከል ባለ አወንታዊ ወይም አሉታዊ ግንኙነት ላይ ተመስርቶ ማጥናት የተሻለ ነው።
መቻቻል ከሚታይባቸው ጉዳዮች መካከል የተለያየ ሃይማኖት ተከታይ ቡድኖች ይገኙበታል። ይህም የሃይማኖት መቻቻል ጽንሰሀሳብ በሚል ይታወቃል። በሃይማኖት መቻቻል ጽንሰሀሳብ መሰረት "የሌሎችን ሃይማኖት ከራሳችን ሃይማኖት ጋር በማንኛውም መለኪያ ብናነፃጽረው 'መጥፎ ነው!' የምንልበት መለኪያ የለንም" (ኒውማን፣ 1978)። ሃይማኖታዊ መቻቻል በአንድ አካባቢ በጉርብትና በሚኖሩ በተለያየ የሃይማኖቶች ተከታይ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል የሚፈጠር የመቻቻል አንዱ ገጽታ ሲሆን የፎክሎር አንዱ አብይ ዘርፍ በሆነው በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ የሚጠና ነው። መቻቻልና አብሮነት የተያያዙ ጽንሰሀሳቦች ናቸው። አብሮነት ሁለት ቡድኖች ልዩነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድነት ሲኖሩ የሚፈጥሯቸው የጋራ ጉዳዮች ሲገናኙ የሚኖረውን ግንኙነት ሰላማዊነት የሚያሳይ ነው። መቻቻል ደግሞ በሁለት ቡድኖች ወይም ግለሰቦች መካከል ልዩነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በጋራ ጉዳይ አብሮ መሆንን ያሳያል (ጆን፣ 2001)። ሰዎች አብሮ በመኖር ሂደት ተሞክሮ ያገኛሉ። በተሞክሯቸውም ምን መስራትና አለመስራት እንዳለባቸው ያውቃሉ። "አብሮነት" የተሻለ የኑሮ ግንኙነት ለመፍጠር ማህበራዊ መተሳሰብን ለማጠናከርና አካባቢን ምቹ ለማድረግ የሚያግዝ የመቻቻል ባሕርይ ነው (ጆን፣ 2001)። መቻቻል ሁለትና ከዚያ በላይ ቡድኖች መኖራቸውን የሚያመለክት ሲሆን ቡድኖቹ በሰላም አብረው ለመኖር አንዱ የሌላውን እምነት አክብሮ መገኘትንም ያሳያል።

እንደ ሩቂያ (2018) ገለጻ የወሎ ማህበረሰብ የሀይማኖት መቻቻል ለሌላው ዓለም ምሳሌ ሊሆን የሚችል ነው። በወሎ ማህበረሰብ ሃይማኖታዊ መቻቻል ተቀባይነት ያለው እና ባህል መሆን የቻለ እሴት ነው። በመሆኑም ማህበረሰቡ ተቀብሎ ለዘመናት ሲያስቀጥለው ኖሯል። የወሎ ማህበረሰብ በንግግር ደረጃ ማድነቅ ብቻ ሳይሆን መኖራቸውን አምኖ በመቀበልና በተግባር ደረጃም የመቻቻል እሴትን በእለት እለት ህይወቱ በመተግበር ከፍ ያለ ደረጃ ላይ አድርሶታል።
ማህበረሰቡ የተቀበላቸው የመቻቻል እሴቶች በርካታ ሲሆኑ ከነዚህም መካከል፤-

ሀ. በማህበረሰቡ ዘንድ ሁለቱም እምነት ተከታዮች እኩል ተቀብለው የሚተገብሯቸው እሴቶች አሉ። ሙስሊሙ ወዳጃ የሚለውን እሴት ክርስቲኑም ተቀብሎ ይተገብረዋል። ክርስቲኑ ጸበል የሚለውን ሙስሊሙም ተቀብሎ ይተገብረዋል።

ለ. በማህበረሰቡ ዘንድ ሁለቱም እምነት ተከታዮች በተለያየ ደረጃ ተቀብለው የሚተገብሯቸው እሴቶች አሉ። ለምሳሌ "የአይን ልጅ" የሚባለው ባህል በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ

በባለቤትነት የሚተገበር ሲሆን በተግባር ግን በሁለቱም ዘንድ በተለያየ ደረጃ ይተገበራል፡፡

ሐ. በማህበረሰቡ ዘንድ ሁለቱም እምነት ተከታዮች የማይተገብሯቸው ነገር ግን ትክክል መሆናቸውን የሚያምኑባቸው እሴቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ፤- አመጋገብ፣ ንጽህና አጠባበቅ

መ. በማህበረሰቡ ዘንድ ሁለቱም እምነት ተከታዮች የማይተገብሯቸው ነገርግን የራሳቸው መገለጫ መሆናቸውን የሚምኑባቸው እሴቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ ሀይማኖታዊ ትዕዛዛት በዚህ ስር ይመደባሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡ ሃሳቦችን ሲጠቃለል መቻቻል የሰው ልጅ ሰው ሆኖ በመፈጠሩ ብቻ ባህሉ፣ አስተሳሰቡ፣ አጠቃላይ ማንነቱን ማክበር፣ መቀበል እና ማድነቅ ማለት ነው፡፡ ይህም ሰዎቹ የመቻቻል ቁም ነገር የሚቃወሚቸው ሌሎች ሰዎች ቢኖሩም ሰዎች የግል እምነታቸውን ይዘው አብረው በፍቅር፣ በሰላምና በመተሳሰብ መቀጠል መቻላቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡

### 3.2 የጠቀሜታዊነት ንድፈ ሃሳብ

### (Functional Theory)

የጠቀሜታዊነት የፎክሎር ንድፈ ሀሳብ በአንድ ማህበረሰብ ወይም ፎክ ቡድን ውስጥ ያሉ የተለያዩ ሎሮች ለማህበረሰቡ ወይም ለፎክ ቡድኑ የሚሰጡትን ጠቀሜታ በማሳየት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው፡፡ የንድፈ ሃሳቡ አራማጆች ተረቶች፣ ሚቶች፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ እምነቶችና ሌሎችም ማንኛውም ሎሮች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ፣ ስነልቦናዊ ወይም ሌላ ጥቅም መስጠትና የማህበረሰቡን ፍላጎት ማሟላት ይኖርባቸዋል የሚል አስተሳሰብ ያራምዳሉ፡፡ ፎክሎር በማህበረሰቡ ውስጥ ምን አይነት ትርጓሜና ጠቀሜታ አለው? የሚለው አብይ ጥያቄያቸው ነው፡፡

የጠቀሜታዊነት የፎክሎር ንድፈ ሀሳብን መሰረት በማድረግ በተለያዩ ባለሙያዎች በርካታ የፎክሎር ጠቀሜታዎች ተገልጸዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል የጠቀሜታዊነት ንድፈ ሀሳብ አራማጅ የሆነው ባስኮም (1954) ፎክሎር አራት ጠቀሜታዎች እንዳሉት ይገልጻል፡፡ እነዚህ አራቱ የባስኮም የፎክሎር ጠቀሜታዎች ለማስተማሪያነት፣ በእኛ ላይ ከተፈጠረብን ተጽዕኖ ለማምለጥ፣ ተቀባይነት ያለው ባህርይ ለመቅረጽ እንዲሁም የማህበረሰቡ ባህል ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ ናቸው፡፡ ሌሎችም የዘርፉ ምሁራን ፎክሎር ለእርስ በእርስ ተግባቦት፣ ለማህበራዊ ችግር መፍቻ፣ ለልማት፣ ለማህበራዊ ማንነት መቅረጫ፣ ለማንነት ማሳያ፣ ለርዕዮተ ዓለም ማስፋፊያ ወዘተ እንደሚጠቅም ይገልጻሉ፡፡

## 4. የጥናቱ ዘዴ

### 4.1 የጥናቱ ንድፍ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በደቡብ ወሎ ዞን ቦረና ወረዳ የክርስትናና እስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በአብሮነት ለመኖር ያስቻሏቸው የመቻቻል መገለጫ እሴቶችን በመለየት ማስተዋወቅ ነው፡፡ የጥናቱ ንድፍ ከአይነታዊ ምርምር የሚመደብ ሲሆን ገላጭ የምርምር ስልትን ተከትሎ ተካሂዷል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያቱም የመቻቻል መገለጫ እሴቶችን ለማሳየት ስለሚረዳ ነው፡፡ የጥናቱን ዓላማ ለማሳካትም የዲስኩር ትንተናን እንደጥናት መንገድ ተጠቅሟል፡፡

### 4.2 የመረጃ ምንጭና የንሞና ዘዴ

ጥናቱ የክርስትናና እስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በአብሮነት ለመኖር ያስቻሏቸው የመቻቻል መገለጫ እሴቶችን በመለየት ለማስተዋወቅ ያለመ ነው፡፡ ለጥናቱ የተመረጠው አማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ሲሆን በደቡብ ወሎ ዞን 22 ወረዳዎች ይገኛሉ፡፡ በዞኑ ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል አንዱ ቦረና ነው፡፡ በመሆኑም በጥናቱ በደቡብ ወሎ ዞን ቦረና

ወረዳ የክርስትናና እስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በአብሮነት ለመኖር ያስቻሏቸው የመቻቻል መገለጫ እሴቶችን በመለየት ለማስተዋወቅ ተሞክሯል፡፡ ቦረና ወረዳ የተመረጠበት ምክያትም አጥኚው በወረዳው ውስጥ ከአምስት ዓመት በላይ የኖረ በመሆኑና በክርስትናና እስልምና ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ያለው አብሮነትና የእርስ በእርስ መስተጋብር ትኩረቱን ስለሳበው ለሌሎች ለማስተዋወቅ በማሰቡ ነው፡፡ በመሆኑም ወረዳው በአመቺ የንሞና ዘዴ ተመርጧል፡፡

ጥናቱ ከተጠኘው ህዝብ እይታ አንፃር መረጃ ለማሰባሰብ “ቀዳማይ” የመረጃ ምንጭ (ምልከታ እና ቃለመጠይቅ) እንዲሁም ጽንሰሃሳቡን በሚመለከት ያሉ እይታዎችን ይበልጥ ለመረዳትና ለማጠናከር ዳህራይ የመረጃ ምንጭ (ከተለያዩ ጽሁፎችና መጻህፍት) ተጠቅሚል፡፡ በመሆኑም ለቃለመጠይቅ በታላሚ ንሞና ዘዴ (ከሁለቱም እምነት ተከታይ) ስምንት ሰዎች የተመረጡ ሲሆን ሁሉም መረጃ አቀባዮች ወንዶች ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የሚስተዋሉ ለመቻቻል አስተዋጾ ያላቸውን እሴቶች አስመልክቶ እንዴት እንዲፈጸሙ ዝርዝር መረጃዎች በቃለመጠይቅ አማካኝነት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በተጨማሪም የማህበረሰቡን በመቻቻል አብሮ መኖር ባህልን በሚመለከት በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች (በሰርግ፣ በለቅሶ፣ በጸበል፣ በእድር አውዶች) ላይ በመገኘት መረጃዎችን በምልከታ ለመሰብሰብ ተሞክሯል፡፡

### 4.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በጥናቱ የመቻቻል እሴት መገለጫዎችን በሚመለከት መረጃዎች በምልከታና በቃለ-መጠይቅ ከተሰበሰቡ በኋላ መረጃ አቀባዮቹ የሰጧቸው መረጃዎች በየአይነታቸው ተደራጅተዋል፡፡ በመቀጠልም የክርስትናና እስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በመቻቻል አብረው ለመኖር ያስቻሏቸው የመቻቻል መገለጫ እሴቶች ምንነትና ባህሪያት ለማስተዋወቅ የጥናቱ አይነታዊ ምርምር ንድፍን በመከተል በገለጻ ስልት መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡

## 5. አካባቢያዊ ዳራ

ለጥናቱ የተመረጠው አማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ነው፡፡ በደቡብ ወሎ ዞን 22 ወረዳዎች ይገኛሉ፡፡ በዞኑ ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል አንዱ ቦረና ነው፡፡ የቦረና ወረዳ ከደቡብ ወሎ ዞን ዋና መዲና ደሴ ከተማ 180 ኪ.ሜ ርቀት በምዕራብ፣ ከክልሉ ርዕሰ መዲና ከባህር ዳር 285 ኪ.ሜ ርቀት በምስራቅ እንዲሁም ከአዲስ አበባ 460 ኪ.ሜ ርቀት በሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ ይገኛል፡፡ ወረዳውን ከሚያዋስኑ ጎረቤት ወረዳዎች በምእራብ ምስራቅ ጎጃም ዞን፣ በምስራቅ ለጋምቦ ወረዳ፣ በሰሜን ምስራቅ ሳይንት ወረዳ፣ በደቡብ ወግዲ ወረዳ ያዋስነዋል፡፡

የቦረና ወረዳ ፕላን ኮሚሽን (2015) እስታስቲክስ መረጃ እንደሚመለክተው የቦረና ወረዳ አጠቃላይ የህዝብ ብዛት 200,378 ሲሆን የቆዳ ስፋቱ ደግሞ 1,000 ኪሜ ስኩየር ነው፡፡ የቦረና ወረዳ በ 34 የገጠር ቀበሌዎችና 4 የገጠር ከተሞች የተዋቀረ ነዉ፡፡ በወረዳው ውስጥ የክርስትና (ኦርቶዶክስ ተዋህዶ፣ የመካነ እየሱስ፣ የካቶሊክ እና ጅሆባ ዊትነስ) እና የእስልምና ሃይማኖቶች ይገኛሉ፡፡ በዚህም መሰረት የወረዳው ነዋሪዎች ከእምነት አንጻር 47% የክርስትና (ኦርቶዶክስ ተዋህዶ፣ የመካነ እየሱስ፣ የካቶሊክ እና ጅሆባ ዊትነስ) እና 53% የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው፡፡ በወረዳው ከሃይማኖት ተቋማት አንጻር 240 መስጊዶች 11 የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን፣ 1 የመካነ እየሱስ፣ 1 የካቶሊክ እና 1 ጅሆባ ዊትነስ አምልኮት ቦታዎች (ቤተክርስቲያኖች) ይገኛሉ፡፡
የቦረና ወረዳ ፕላን ኮሚሽን (2015) መረጃ እንደሚያመለክተው በወረዳው ውስጥ 16 የከተማ እና ከ 80 በላይ የገጠር እድሮች /ቅሬዎች/ ይገኛሉ፡፡ እያንዳቸው እድሮች በአማካይ ከ 900 — 1500 አባላት አሉት፡፡ የወረዳው ነዋሪዎች የሃይማኖት

ልዩነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች ምክንያት ህብረት ይፈጥራሉ፡፡ ማህበራዊ ግንኙነቱን ለመፍጠርም ሆነ የተመሠረተው ግንኙነት ቀጣይነት እንዲኖረው የሁለቱም ሃይማኖት ተከታዮች ሚናቸው ተመጣጣኝ ነው፡፡ ማህበራዊ መስተጋብሮቹ በኑሮ ውስጥ አንዱ ወደ ሌላው በተለያዩ ምክንያቶች በመሄድ ይገናኛሉ፡፡

## 6. የሃይማኖት መቻቻል እሴቶች

በደቡብ ወሎ ዞን ቦረና ወረዳ ለአብሮነት አስተዋጽዎ ያላቸው የመቻቻል እሴቶች በርካታ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ የመቻቻል እሴቶች በሠሎሞን (2007) አከፋፈል መሰረት በሁለት ምድብ (ሀገረሰባዊ ልማድ፣ ማህበረፖለቲካዊ ተቋም) ስር ይከፈላሉ፡፡ የማህበረሰቡ ዋና ዋና የመቻቻል እሴቶች ሀገረሰባዊ መድሀኒት፣ ሀገረሰባዊ እምነት፣ ሀገረሰባዊ ጋብቻ፣ እድር፣ ሀገረሰባዊ ዳኝነትና ጅጌ/አዝማች ናቸው፡፡ እነዚህን እሴቶች ከምድቦቻቸው አንጻር ስንመለከታቸውም ሀገረሰባዊ መድሀኒት፣ ሀገረሰባዊ እምነትና ሀገረሰባዊ ጋብቻ በሀገረሰብ ልማድ ስር ይካተታሉ፡፡ ቀሪዎቹ እድር፣ ሀገረሰባዊ ዳኝነትና ጅጌ/አዝማች ደግሞ በማህበረፖለቲካዊ ተቋም ስር የሚመደቡ ናቸው፡፡

### 6.1 ሀገረሰባዊ ልማድ

#### ሀ. ሀገረሰባዊ መድሀኒት

ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው መንፈሳዊ የህክምና ግብዓቶችን በመጠቀም የጤና ችግሮችን ለመፍታት የሚከወኑ ድርጊቶች የሀገረሰብ ህክምና ስር ይመደባሉ፡፡ በዚህም የተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ በሚገኙ እምነቶችና ሀይማኖቶች የአስተምህሮ ስርዓት መሰረት እንደመስቀል፣ የሀይማኖት መጽሐፍ፣ ጸበል፡ ዘምዘም፡ ክታብ ወዘተ በመጠቀም በቅዱስ ስፍራዎች እንደ ቤተክርስቲያን መስጊድ፣ የጸበል ቦታ፡ ሀገረሰባዊ ሀይማኖቶች የሚከወኑበት ስፍራ ወዘተ ትልቅ ስፍራ በሚሰጣቸው ግለሰቦች በሚደረጉ ጸሎቶች፣ ለፈጣሪያቸው ወይም ሌላ ህመምን ያመጣል ብለው ለሚያምኑበት አካል በሚያቀርቧቸው መስዋዕቶችና መሰል መንፈሳዊ ድርጊቶች አማካኝነት የተለያዩ በሽታዎችን የመለየትና የመፈወስ ስርዓቶች ያካሂዳሉ (ሠሎሞን፣ 2007)፡፡

በቦረና ወረዳ በርካታ የጸበል ስፍራዎች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ሚካኤል፣ ትልክ ድንጋይ፣ ቅድስት አርሴማ፣ ምስካቤ ቅዱሳን፣ አማኑኤል፣ አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ፣ ልደታ ማሪያም፣ ኪዳነምህረት፣ ዳቦገዳም መድሃኒዓለም፣ ገብረክርስቶስ ወዘተ ይጠቀሳሉ፡፡

በቦረና ማህበረሰብ የጤና እክል የገጠመው ወይም እርኩስ መንፈስ የተጠናወተው፣ አጋንንት የለከፈው ወዘተ ክርስቲያኑም ሆነ ሙስሊሙ በልቡ አምኖ ጤንነቱን ለማግኘት ወደነዚህ የፀበል ቦታዎች ይሄዳል፡፡ ከጸበላቸው አልፎ እምነታቸውን ይቀበላል፤ በመስቀሎቻቸው ይታሻል፡፡ እንደ ቀሲስ ፍቅረማሪያም (ቃለመጠይቅ መጋቢት16/2016) ገለጻ፣ ጸበል መጠመቅ በክርስትናው በኩል የሚገኝ እምነታዊ-ሀይማኖታዊ ህክምና ሲሆን አገልግሎቱ የሚሰጠው ለሙስሊሙም ጭምር ነው፡፡ ይሄውም ክርስቲያኑ ለሃይማኖታዊ ስርዓቱና ለጤንነቱ ሲል የሚፈጽመው ሲሆን ሙስሊሙ ደግሞ ለጤንነቱ ፈውስ ማግኛ ሲል የሚገለገልበት ነው፡፡

ሙስሊሞቹ ይህንን የሚያደርጉት ቅድመ አያቶቻቸው፣ አያቶቻቸውና አባቶቻቸው በዚህ ፎክሎራዊ እሴት ተጠቅመው መፈወሳቸውን ስለሚያውቁ ነው፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳ ኋላ ላይ ተምረውና አምነው ሀይማኖቱን ለመቀበል የሚጠመቁ ቢኖሩም እንኳ ጸበል መጠመቅ ለብዙሃኑ ሙስሊሞች ሃይማኖታዊ ጉዳይ ሳይሆን ባህል፣ ወግና ልማድ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ጸበል መጠመቅ የሙስሊሙም የክርስቲያኑም የጋራ እሴት ነው (አቶ ዩሱፍ፣ ቃለመጠይቅ የካቲት 12/2016፤ አቶ ብርሀኑ ቃለመጠይቅ የካቲት

23/2016)፡፡ በመሆኑም በቦረና የጸበል ቁምነገሩ ጸበሉን የሚጸበለው አካል ክርስቲያን ወይም ሙስሊም መሆኑ ሳይሆን፣ በጸበሉ ተጠምቆ ለመፈወስ ያለው ልባዊ ፍላጎት ነው (ቀሲስ ፍቅረማሪያም፣ ቃለመጠይቅ መጋቢት16/2016፤ አቶ ብርሀኑ፣ ቃለመጠይቅ የካቲት 23/2016)፡፡ በመሆኑም በቦረና የሚገኙ ሙስሊሞች በሁሉም የጸበል ቦታዎች (ከገብረክርስቶስ ጸበል በስተቀር) ገብተው ይጠመቃሉ፤ አጥማቂ ካህናትም የጥምቀት አገልግሎቱን ያለምንም ልዩነት ይሰጣሉ፡፡ ሆኖም ገብረክርስቶስ ጸበል ገብቶ ለመጠመቅ የክርስትና እምነት ተከታይ ሆኖ መገኘት የግድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም ጥቂት በአካባቢው የሚገኙ የእስልምና እምነት ተከታዮች ጸበሉን በክርስቲያን ወዳጆቻቸው አማካኝነት አስመጥተው ይጠጣሉ፤ ይቀባሉ፡፡ ይህም የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ወደ ቦታው አለመሄድ ሳይሆን የአጥማቂያን እምነት የማስቀየር ግለሰባዊ ፍላጎት መሆኑን ነዋሪዎች ይገልጻሉ፡፡ በአጠቃላይ ሲታይም የጸበል ቦታው 2013 ዓ.ም የተጀመረ ከመሆኑ አንጻር ቀደም ባሉ ዓመታት በጸበል ተጠምቆ የመዳን እሴቱ ለክርስቲያንና ለሙስሊም ያለምንም ልዩነት ይፈጸም እንደነበር ያሳያል፡፡

### ለ. ሀገረሰባዊ እምነት

ማህበረሰቡ መልካም ህይወት ለመኖር ይጠቅመኛል ብሎ በዕለት ዕለት ሕይወቱ የሚከውናቸው፣ እንዲህ ቢሆን ችግር ይገጥመኛል ብሎ የሚፈራቸው፣ ይህን ባደርግ ደግሞ የተሻለ ነገር ይገጥመኛል በሚል የውስጥ መንፈሳዊ እምነት የሚከውናቸው በርካታ ልማዶች አሉ፡፡ የእነዚህ ሀገረሰባዊ እምነቶች መነሻቸው ሃይማኖታዊ ሳይሆን የማህበረሰቡ ባህል ነው፡፡

በሀገረሰባዊ እምነት ዘርፍ ስር የሚመደቡት በማህበረሰቡ ውስጥ የተለያዩ ተፈጥሯዊ ሁነቶችን ለምሳሌ ዝናብ፣ ፀሐይ፣ በረዶ፣ መብረቅ ወዘተ ሀይል አላቸው (ማዘዝ ይችላሉ) ተብለው በሚታመኑ ግለሰቦች አማካኝነት የሚከወኑ እምነቶች ናቸው፡፡ በአገራችን ተፈጥሮን ለመቆጣጠር በሚል የሚከወኑ ሀገረሰባዊ እምነቶች በርካታ ናቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል በክረምት ወቅት በረዶ እንዳይጥልና ሰብል እንዳያበላሽ በሚል የሚሰራ ተፈጥሮን የመቆጣጠሪያ አስማት (ጸሎተ በረድ) በሚል የሚደረግ ጸሎት አለ (ሠሎሞን፣ 2007)፡፡

በቦረና የሚገኙ ማህበረሰቦችም በአካባቢያቸው የሚከሰቱ የበረዶና የዝናብ መብዛት ችግሮችን ለመቅረፍ ሀገረሰባዊ እምነቶችን ይተገብራሉ፡፡ በወረዳው ቆላማ አካባቢ የሚገኙ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በአንድ ላይ የበረዶ (የበላ) ጠባቂ በሚል ገንዘብ አዋጥተው በአካባቢው ወደሚገኝ የታወቀ ቦታ (እንደ ደባት መስጊድ ያሉ ሀይማኖታዊ ቦታዎች) በመሄድ ያዋጡትን ገንዘብ ሰጥተው በጋራ ጸሎት አድርገውና አስደርገው ይለያያሉ፡፡ በደጋው አካባቢው ደግሞ በአካባቢው ወደታወቁ የበረድ ደጋሚዎች፣ ጠባቂዎችና ቂጣ ሰቃዮች በመሄድ ያዋጡትን ገንዘብ በመስጠት እምነት ስርዓቱን ያስፈጽማሉ፡፡ በመጨረሻም ምርቱ ተሰብስቦ ሲያልቅ የበረድ ጠባቂ ተብሎ እህል ተሰብስቦ ይሰጣል (አቶ አህመድ እና አቶ የሱፍ፣ ቃለመጠይቅ የካቲት 12/2016)፡፡ ይህም ማህበረሰቡ ሙስሊምና ክርስቲያን አንድ ሆኖ በመቻቻል እንዲዘልቅ አስተዋጾ አለው፡፡

### ሐ. ሀገረሰባዊ ጋብቻ

ጋብቻ በክርስቲያኑም በሙስሊሙም ማህበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ ቦታ አለው፡፡ በቦረና ማህበረሰብ የክርስትና ወይም የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ መሆን የጋብቻ መስፈርት የማይሆንበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ በቦረና የሙስሊም ልጅ የክርስቲያን ልጅ፡ የክርስቲያን ልጅ የሙስሊም ልጅ ታገባለች፤ ያገባል፡፡ በዚህ ሂደት በጋብቻ ወቅት ወይም ኋላ ሙስሊሙ ወደ ክርስትና ወይም ክርስቲያኑ ወደ እስልምና ሃይማኖት ይቀይራል፡፡

አልያም ሁለቱም የየግል ሃይማኖታቸውን እንደያዙ በጋብቻ ተጣምረው አብረው ይኖራሉ፡፡

ሙስሊሙ ከክርስቲያኑ፤ ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ ጋር ይጋባል፡፡ ማህበረሰቡ ጋብቻ ለመፈጸም ምናልባት ዘር ይቆጥር ይሆናል፡፡ ዘር የሚቆጠሩበት ምክንያት አንዱ ለአጥንት ጉዳይ ሲሆን ሌላው ደግሞ በስጋ ዝምድና የማይገናኙ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ከአጥንት ጉዳይ ጋር ተያይዞ የቡዳ ወይ የባሪያ ዘር አለመኖሩን ያረጋግጣሉ:: ከዚህ ውጪ በአጥንቱም በሃብቱም ይመጥናል ለሚለው እስላሙ ለክርስቲያኑ፣ ክርስቲያኑ ለእስላሙ ልጁን ይድራል፤ ይዋለዳል፡፡ በሠላምና በፍቅር በጋራ ይኖራል፡፡ በቦረና በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ግማሹ ሙስሊም ግማሽ ክርስቲያን ሆኖ ይኖራል፤ ባል ወይም ሚስት አንዱ የቄስ ሌላው የሼህ ልጅ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እንዲህ በፍቅር በመኖር የወለዷቸውም ልጆች የመረጡት ሀይማኖት ተከታይ ሆነው ያድጋሉ፤ እንደምርጫቸው ሙስሊም ወይም ክርስቲያን ሊያገቡና ሊወልዱም ይፈቀድላቸዋል (አቶ አህመድና አቶ የሱፍ፣ ቃለመጠይቅ የካቲት 12/2016)፡፡

በቦረና እስላም ከክርስቲያኑ ጋር ተጋብቶ ተዋልዶ ይኖራል፡፡ በቦረና የጋብቻ ባህል የሃይማኖት አባቶችና የእምነቶቹ ተከታዮች የልዩነት ሳይሆን፤ የአንድነት ተግባራዊ መገለጫ ሆነው ቆይተዋል፡፡ በመሆኑም የጋብቻ መስፈርት በቦረና የሃይማኖት መቻቻል አሴት መገለጫ ተምሳሌት ነው (ቀሲስ ፍቅረማሪያም፣ ቃለመጠይቅ መጋቢት16/2016 እና አቶ የሱፍ፣ ቃለመጠይቅ የካቲት 12/2016)፡፡

## 6.2 ማህበረ ፖለቲካዊ ተቋማት

### *ሀ. ሀገረሰባዊ ዳኝነት*

በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ወንጀሎችና ግጭቶች ተባብሰው የከፋ አደጋ ከማድረሳቸው በፊት በአካባቢው በሚታወቁና በጋራ ስምምነት በተመረጡ የሀገር ሽማግሌዎች መፍትሄ እንዲያገኙ ይደረጋሉ፡፡ ሽምግልና በሀገረሰባዊ የዳኝነት ተቋም ስር ይመደባል፡፡ ሀገረሰባዊ የዳኝነት ተቋማት ለማህበረሰቡ ዘላቂ ሰላም በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው (ሠሎሞን፣ 2007)፡፡

በቦረና ማህበረሰብ ውስጥም ሽምግልና በአካባቢው የሚከሰቱ የስርቆት፣ የንብረት ማጥፋት፣ የጸብ፣ የግድያና መሰል ወንጀሎችን የፈጸሙ ግለሰቦች ባህሉ በሚፈቅደው መሰረት ወንጀል ፈጻሚዎችን የማውጣጣት፣ የመቅጣት፡ የማስታረቅ ስራዎችን በመስራትና የተከሰቱ ችግሮችን በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍትሄ በመስጠት ሠላም እንዲሰፍን ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ በቦረና የሽምግልና ስርዓት ሽማግሌዎች በአዋቂነታቸው፣ በታማኝነታቸው፣ በትዕግስታቸው፣ በማህበራዊ ደረጃቸውና በኢኮኖሚ አቅማቸው መሰረት ይመረጣሉ፡፡ ሽማግሌዎቹን ለመምረጥ እስላም ወይም ክርስቲያን መሆን በመስፈርትነት አይወሰድም፤ እስላምም ክርስቲያንም ሊመረጥ ይችላል፡፡ ሽማግሌዎች ወንጀሉን፣ በደሉን ማን እንደፈጸመው ለማወቅ መሃላ በማስፈጸም፣ ጥፋተኛን በመራገም ወዘተ የተደበቀ ወንጀለኛንና በዳይን ይለያሉ፡፡ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘውን ወገን ይቀጣሉ፤ ተጎጂውንም ወገን ካሳ ያስክሳሉ፡፡ ይህም ያለምንም የሀይማኖት ልዩነት ማህበረሰቡ ተቻችሎ በአብሮነት እንዲኖር አስችሎት ቆይቷል (አቶ አህመድና አቶ የሱፍ፣ ቃለመጠይቅ የካቲት 12/2016)፡፡

በቦረና ማህበረሰብ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶች ዳኝነት የሚያገኙበት ሌላው ሀገረሰባዊ የዳኝነት ተቋም “አቡወለድ” በመባል ይታወቃል፡፡ “አቡወለድ” አንድ የዘር ግንድ ያላቸው ሰዎች የሚመሰርቱት ተቋም ነው፡፡ እንደ አቶ አህመድ ገለጻ፣ የአንድ ሰው ዘር ግንድ በአራት አቅጣጫ (በአባቱ አባት፣ በእናቱ አባት በአባቱ እናት እና በእናቱ እናት) ይወሰናል፡፡ በመሆኑም ሰውየው በነዚህ አራት አቅጣጫዎች ዘሩን በማጥናት “አቡወለድ” ማህበር ይመሰርታል፡፡ ይህ “አቡወለድ” ማህበር

ሙስሊሙም ክርስቲያኑም ከየቦታው ተጠራርቶ በየአመቱ (በየመንፈቁ) እየተገናኘ ይገባበዛል፣ ይወያያል፤ የተቸገሩ ወገኖቹን ይረዳል፤ ያጋጠሙ ችግሮችን ይፈታል። አቡወለድ ማህበራት የሚመሰረቱበት ዓላማ በዘመዳሞች መካከል ጋብቻ እንዳይፈጠር መጠበቅ ነው። ሆኖም አብሮ በመኖር ሂደት የአቡወለድ አባል ጋር ግጭት ሊፈጠርና ፀብ ሊመጣ ይችላል። በቦረና በአቡወለድ አባላት መካከል የተፈጠረን ግጭት፣ ጸብ፣ ቅያሜ ለመፍታት የሀገር ሽማግሌ መምረጥ አያስፈልግም። ይልቁንም ተበዳይ ለአቡወለድ አባላቱ መንገር ብቻ ይበቃዋል። በዚህ ጊዜ አቡወለዱ ጉዳዩን አጣርቶ ችግሩን ከስር መሰረቱ እንዲፈታ (እንዲደርቅ) ያደርጋል (አቶ አህመድ ቃለመጠይቅ የካቲት 12/2016፤ አቶ ተድላና አቶ ካሳው ቃለመጠይቅ የካቲት 14/2016)።

እንደ አቶ አህመድ (ቃለመጠይቅ የካቲት 12/2016) ማብራሪያ በቦረና ማህበረሰብ የአቡወለድ አባል ለመሆን እስላም ወይም ክርስቲያን መሆን መስፈርት አይደለም። አቡወለድ በአካባቢው ሙስሊምና ክርስቲያን አማኞች በዘር ሀረጋቸው (የደም ትስስር) ብቻ በመቻቻልና ችግራቸውን በጋራ በመፍታት በአብሮነት ለመኖር ያስችላቸዋል፤ ያስተሳስራቸዋል።

## ለ. ቅሬ/እድር

“ቅሬ” እድር እየተባለ ከሚጠራው ማህበራዊ ተቋም ጋር ተመሳሳይ ዓላማ ያለው ሲሆን የሚተዋወቁ ሰዎች በፈቃደኝነት የሚመሠርቱት ማህበረ-ባህላዊ ተቋም ነው። ቅሬ እንደ እድር ሁሉ ከሃዘንና መከራ ጋር ይገናኛል። ቅሬ ከእድር የሚለየው ቅሬው ከቀብር መልስ እንጀራና ወጥ የሚያመጣው ከየቤቱ መሆኑ ነው። ከለቅሶ ባሻገር ቅሬም ሆነ እድር ሌሎች የተለያዩ ማህበራዊ ፋይዳዎች፣ ደንብና ስርዓቶች አሏቸው። ለምሳሌ አቅም በፈቀደ መጠን በሃዘን ጊዜ ከቅሬ እንደማይቀር ሁሉ፣ በደስታ (በሠርግ) ወቅት ቅሬ አይለይም፤ በሁለቱ አካላት መካከል ፀብ (ቂም) ቢኖር እንኳን እርቅ ወርዶ የሃዘንም ሆነ የደስታ ተካፋይ እንዲሆኑ ይደረጋል። በተለይ በሃዘን ወቅት ያኮረፈው ከነኩርፊያው በጸበኛው ሰው ሃዘን ላይ ይገኛል።

አንድ እድር ሲመሰረት መስራቾቹ ከመተዋወቅ አልፎ የጋራ ፍላጎት ያላቸው ናቸው። ፍላጎቱ የሚመጣው በመቀራረብና አንዱ ሌላውን በማክበር በመተሳሰብ አንዱ ለሌላው መኖር እውቅና በመስጠት የሚጠነክር ነው። ዕድሮች በአባላት የመኖሪያ ሠፈርና በጾታ ላይ መሠረት አድርገው ይደራጃሉ ወይም ይቋቋማሉ። የወንድ፣ የሴት፣ የሰፈር፣ የከተማ የሚሉ የዕድር ዓይነቶች አሉ። ሞት ድንገት ሲመጣ የሰው ልጅ አጋዥ ያስፈልገዋል። በማህበረሰቡ ባህል አንድ ሰው ሲሞት በብዙ ሰው አጀብ አስከሬን ወደ መቃብር በክብር ይሸኛል። የእንግዳ መሸኛ ድንኳን ይሠራል። የሚችን የቅርብ ዘመዶች ያስተዛዝናል፤ ገንዘብ በማዋጣት ወጭውን ይጋራል። ይህን ማህበራዊ ኃላፊነት መወጣት ደግሞ የእድሮች ነው። እድር/ቅሬ በቦረና ማህበረሰብ የክርስቲያኑና የሙስሊሙ የጋራ ማህበራዊ ተቋም ነው። በዚህ መሰረት በቦረና ክርስቲያኑም ሙስሊሙም ለብቻው ቅሬ ወይም እድር የለውም። ሁለቱም በአንድ ቅሬ ውስጥ ይሳተፋሉ (አቶ አህመድና አቶ የሱፍ ቃለመጠይቅ የካቲት 12፣ ቀሲስ ፍቅረማሪያም መጋቢት16/2016)።

በቦረና የመጀመሪያዎቹ እድሮች መቼ እንደተመሰረቱ ባይታወቅም እስካሁን የነበረው ቀጥሎ አዳዲስ እየተመሰረቱ በርካታ እድሮች ለተመሳሳይ ዓላማ በተለያየ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ዘልቀዋል። በድሮ ጊዜ ዕድሮቹ በቃል በሚተላለፉ ተግባራትና ደንቦች ነበሯቸው። በአሁኑ ጊዜ ደግሞ እያንዳንዱ ዕድር በፅሁፍ የሰፈረ መተዳደሪያ ደንብ አላቸው። እድር/ቅሬ በቦረና ማህበረሰብ የክርስቲያኑና የሙስሊሙ የጋራ ማህበራዊ ተቋም ነው።

ማህበረሰቡ በአንድ ቅሬ ውስጥ ሲሰባሰብ የቅሬው ዳኛ ሙስሊሙ ወይም ክርስቲያኑ ሊሆን ይችላል፡፡ በቅሬው የአሰራር መርህ መሰረት ክርስቲያኑም ሆነ ሙስሊሙ በወቅቱ ያለው የእድር ዳኛ ይቀጣዋል፡፡ ማህበረሰቡም ያለምንም የሀይማኖት ልዩነት ቅጣቱን አሜን ብሎ ይቀበላል እንጂ የእድር ዳኛውን ማንነት በማንሳት ቅሬታ ውስጥ አይገባም፡፡ በቦረና ክርስቲያንና ሙስሊም በቅሬ/እድር አንድ ሆኖ በመቻቻል ለመኖር በዚህ እሴት ተያይዟል፡፡

## ጂጌ/ አዝማች

ጅጌ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ግለሰቦች ተሰባስበው የሚመሰርቱት ማህበራዊ ተቋም ነው፡፡ ተቋሙም በአንድ ግለሰብ ብቻ ሊሰሩ የማይቻሉና ጊዜና ጉልበት የሚወስዱ ከባድ ስራዎችን በጋራ ተባብሮ መስራት (የአንድ ግለሰብን ማሳ በጋራ ማረስ፣ የደረሰ ሰብልን በጋራ ማጨድና መሰብሰብ፣ የግለሰብን ወይም የአካባቢው መሪ የሆኑ ግለሰቦችን መኖሪያ ቤቶችና የእምነት መፈጸሚያ ቤቶችን በጋራ መስራት የመሳሰሉትን) የሚያስችል ማህበራዊ ተቋም (እንደ ሠሎሞን 2007 አከፋፈል አንዱ ማህበረፖለቲካዊ ተቋም) ነው፡፡

ማህበረሰቡ እንደሚገልጸው ወንፈል ሁለትና ከሁለት በላይ በአብዛኛው የአንድ አካባቢ ነዋሪዎች ተራ ገብተው የተለያዩ ስራዎችን የሚያከናውኑበት የስራ ባህል ነው፡፡ ይህም ዛሬ የአንዱን፣ ነገ የሌላውን፣ ተነገ ወዲያ የዚያኛውን ስራ ማከናወን ማለት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ወንፈል የስራ ብድር ማለት ነው፡፡ ብድር ስለሆነም አንዱ የሌላውን ብድር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ ክፍያውም የመጀመሪያው ግለሰብ እንደሁኔታው ካቀረበው ጉልበቱና መስተንግዶው ሌላ ይዞት የመጣውን የስራ መሳሪያ ሁሉ ይጨምራል፡፡ በተቃራኒው ጅጌ ስራ የሰራልን አካል እንድናግዘው ካልጠራን በስተቀር እንደወንፈል አይቆጠርም፡፡ በቦረና ቀደም ባሉት ዘመናት ሙስሊሙና ክርስቲያኑ በአንድነት በጂጌ መስጊድና ቤተክርስቲያን ለመስራት በጉልበትና በገንዘብ ሲደጋገፉ ኖረዋል፡፡ በበዓላቶቻቸው ላይም በእምነት ቦታዎች ላይ በመገኘት ደስታቸውን ሲገላለጹ ቆይተዋል (አቶ እስማኢል፣ ቃለመጠይቅ የካቲት 14/2016፤ አቶ ብርሀኑ ቃለመጠይቅ የካቲት 23/2016)፡፡

በቦረና ማህበረሰብ በትብብር መስራትን ከሚያበረታቱ ማህበረባህላዊ ተቋማት መካከል አንዱ "አዝማች" ነው፡፡ አዝማች በአካባቢው አንድ ሰው ልጁን ሲድር ሌላው ሰው በሰርጉ እለት ከ80-100 ሰዎችን የድግስ መስተንግዶ ወጪ (እንጀራ፣ ስጋ/ክክ ወጥ/፣ ጠላ/ቀሪቦ የዝግጅትና መስተንግዶ ጉልበት) በሙሉ ሸፍኖ ኃላፊነትን መወጣት ነው፡፡ በዚህም ባለድግሱ ልጁን ሲድር ብዙው የድግስ ወጪ አዝማች በሚይዙ ወዳጆቹና ጎረቤቶቹ ይሸፈንለታል፡፡ ከእሱ የሚጠበቀው ስንት አዝማች እንዳለው ቆጥሮ ለድግሱ የሚመጥን ሰው (ክርስቲያንም ሙስሊምም) በሰርጉ ላይ እንዲታደም መጥራትና ለባለ አዝማቾች የምስጋና ግብዣ ማዘጋጀት ብቻ ነው (አቶ ዩሱፍ እና አቶ አህመድ፣ ቃለመጠይቅ የካቲት 12/2016)፡፡

እንደ አቶ አህመድ እና አቶ ዩሱፍ (ቃለመጠይቅ የካቲት 12/2016) ማብራሪያ፣ ይህ ባለጉዳይ ግለሰብ ታዲያ ይህን አዝማች የቱንም ያህል ጊዜ ቢቆይ ብድሩን የሚመልሰው አዝማች የያዘለት ጎረቤት ወይም ወዳጅ ልጁን ሲድር ነው፡፡ እርሱም በተራው አዝማች ይዞ ድግሱን በመደገስ ከ80-100 ሰው አብልቶ ብድሩን ይመልሳል፡፡ ሆኖም የአዝማች እዳ ያለበት ሰው ያ ጎረቤቱ ልጅ ሲድር በወቅቱ ካለው ሁኔታ አንጻር ችግር ላይ ቢሆን /ቢቸገር/ ከባለጉዳዩ ጋር በመመካከር አዝማቹን እንዲያወጣ አይገደድም፡፡ ባለጉዳዩ ሰው በርካታ አዝማች የሚኖረው ከሆነ በመመካከር አንድ አዝማች ሊያወጣ የሚችለውን ገንዘብ ተሰልቶ ለባለጉዳዩ በጥሬ ገንዘብ በመስጠት እዳውን ሊከፍል ይችላል፡፡

በቦረና ባህል መሰረት አዝማች ለማውጣት ክርስቲያን ወይም እስላም መሆን መስፈርት አይደለም፡፡ ክርስቲያኑ፤ ሙስሊሙ ልጁን ሲድር፣ ሙስሊሙም ክርስቲያኑ ሲድር አዝማች ይዞ ከባለጉዳዩ ጋር በመነጋገር ሰርግ የተጠሩ እንግዶችን ያበላል፡፡ አዝማች የሚያወጣው ሰው እንደ አስፈላጊነቱ (እንደተመደበበት) ለሙስሊም ወይም ለክርስቲያን እንግዶች ድግስ ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡ ይህም ሙስሊምና ክርስቲያን አማኞች በመቻቻልና አብሮነት ለመኖር አስችሏቸዋል (አቶ ዩሱፍ እና አቶ አህመድ ቃለመጠይቅ የካቲት 12/2016፣ አቶ እስማኢል፣ ቃለመጠይቅ የካቲት 14/2016)፡፡

## 7. ማጠቃለያና ይሁንታ

ጥናቱ በደቡብ ወሎ ዞን ቦረና ወረዳ የክርስትናና እስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በአብሮነት ለመኖር ያስቻሏቸው የመቻቻል መገለጫ እሴቶችን በመለየት ማስተዋወቅ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ጥናት በአብዛኛው ለአብሮነት መሰረት በሆኑ እሴቶችና የእሴቶቹ ባለቤት በሆነው ማህበረሰብ አኗኗር ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በመሆኑም ትኩረቱን በመቻቻል፤ በመከባበር፣ በመተባበር፣ በመተሳሰብ፣ በመተዛዘን፣ በመረዳዳትና በመደጋገፍ ላይ አድርጓል፡፡ አብሮ በመሥራት፣ አብሮ በመብላትና አብሮ በመጠጣት ላይ ያተኩራል፡፡

በዚህ መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በቦረና፣ በሙስሊምና ክርስቲያን ማህበረሰብ እንዴት እንደሚገለጽ ተጠንቷል፡፡ እንዲሁም ከማህበራዊ ኑሮ መስተጋብር አንጻር የሃይማኖት መቻቻል እሴት በቦረና ማህበረሰብ ምን ማለት እንደሆነና ምንን እንደሚያሳይ ተተንትኗል፡፡ ይህም የተደረገው የጥናቱን ጽንሰ-ሃሳብ፡ ንድፈ-ሃሳብና የጥናቱን ዘዴዎች መሰረት በማድረግ ነው፡፡

ከጽንሰ-ሃሳብ አንፃር ፎክ ማለት በአንድ በሆነ የጋራ እሴት የተሳሰሩና የሚገናኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው የሚለው የዳንደስ (1965) መርህ ለዚህ ጥናት መነሻ መሰረት ሆኖ አገልግሏል:: "ሎር" የሚለው መርህ ደግሞ "የሰው ልጅ በማህበር ሲኖር የፈጠራቸውና የሚጠቀምባቸው የአሰራር፡ የአኗኗር፣ የአስተዳደር፣ የአመጋገብ፣ የአለባበስ ወዘተ ዘዴዎች፣ ብልሃቶች፡ ፍልስፍናዎች፣ ጥበቦች፣ አመለካከቶች፣ እምነቶች፣ አምልኮዎች ወዘተ የሚለው የዶርሰን (1972) አስተሳሰብ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ከዚህም ሌላ የእሴቶቹን ትርጉም፣ ምንነት፣ ፋይዳ፣ ተግባርና ጥቅም ተረድቶ፣ የማህበረሰቡን ስሜት፣ አስተሳሰብ፣ እምነት፣ ማንነት፣ ፍልስፍና፣ አመለካከት ወዘተ ተገንዝቦ፣ በዚያው በአካባቢው፣ በባህሉና በማህበረሰቡ ኑሮ ላይ ተመስርቶ መረጃዎቹን ለመሰብሰብና ለመተንተን እንዲቻል፤ ጥናቱ በጠቀሜታዊነት የፎክሎር ንድፈሃሳብ መርህ ተመርቷል፡፡

የጥናቱም ዘዴም አይነታዊ ነው፡፡ በዚህ ዘዴ የተሰበሰቡት መረጃዎች ከተለያዩ ጉዳዮች ጋር እየተዛመዱ ገላጭ የምርምር ስልት ተተንትነዋል፡፡ የተተነተኑት መረጃዎችም ከባለቤቶቹ መንጭተው እዚያው የተቀዱና በባለቤቶቹ ድምጽ ላይ የተመሰረቱ ናቸው:: በመሆኑም በተደረገው ምርምር የቦረና ማህበረሰብ ልዩ ልዩ የሃይማኖት መቻቻል ስልቶችና ከስልቶቹ የሚመነጩ በርካታ የጋራ እሴቶች (ሀገረሰባዊ መድሀኒት፣ ሀገረሰባዊ እምነት፣ ሀገረሰባዊ ጋብቻ፣ እድር፣ ሀገረሰባዊ ዳኝነትና ጅጊ/አዝማች) እንዳሏቸው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በጥናቱ ውጤት መሰረትም የመቻቻል እሴቶቹ በተለይም በእስልምናና በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች መካከል "መቻቻል" የሚለውን ፅንሰ-ሀሳብ፣ መርህና ተግባራዊ ድርጊቶች የሚያካትቱ ገጽታዎችን (አንዱ የሌላውን ህልውና ተቀብሎ እውቅና መስጠትን፣ መተሳሰብን፣ መረዳዳትን፣ መተባበርን፣ አብሮነትን፣ አንድነትንና

ሰላምን ወዘተ) ለማምጣት አወንታዊ ጠቀሜታ እንዳላቸው ተመላክቷል፡፡

ከጥናቱ ውጤት በመነሳት የሚከተሉት የይሁንታ ሀሳቦች በአጥኚው ተሰንዝረዋል፡፡

1. የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች መማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች መቻቻልን የሚያሳዩ ባህላዊ እሴቶችን በንባብ ማስተማሪያ ቴክስትነት፣ ቲያትር አዘጋጆችም እሴቶችን በጭብጥነት በማካተት ለታዳጊ ልጆች ቢያስተዋውቁ፤
2. የመቻቻል እሴቶች በተለያዩ ምክንያቶች እየተሸረሸሩና እየተዳከሙ በመሄድ ላይ እንደሆኑ የእሴቶቹ ባለቤቶች ይናገራሉ፡፡ በመሆኑም ምክንያቶቹን ከስረ-መሰረታቸው አውቆ መፍትሄ ለማበጀት በርዕሰ-ጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ጥናትና ምርምር ቢካሄድ፣
3. በቦረና የሃይማኖት መቻቻል እሴቶች ከጊዜ ወደጊዜ እየተረሱ ነው፡፡ በመሆኑም ታዋቂ ግለሰቦች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ አካላት ትውልዱ እሴቶቹን እንዲያውቃቸው፣ እንዲጠብቃቸው እና እንዲጠቀምባቸው በኃላፊነት ቢያስተምሩ፣

## ዋቢ ጽሁፎች


ሠሎሞን ተሾመ፡፡ (2007)፡፡ *ፎክሎር፤ ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ፡፡* አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

አጸደ ተፈራ፡፡ (2007)፡፡ የዋግ ኽምራ የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት ስነ-ስርዓት ፋይዳ ትንተና፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት /ያልታተመ/፡፡

ቦረና ወረዳ ፕላን ኮሚሽን፡፡ (2015)፡፡ አጠቃላይ እስታስቲክስ መረጃ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ደስታ ተክለ ወልድ፡፡ (1962)፡፡ *አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡* አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ፡፡

ጌታዋ ሞላ፡፡ (2008)፡፡ የሃይማት መቻቻል እሴት በወሎ፤ ምንጩ፣ መገለጫዎቹና ተግባሩ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት /ያልታተመ/፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ (1991)፡፡ *የስነ-ቃል መምሪያ፡፡* አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ፍሬህይወት ባዩ፡፡ (June 2018)፡፡ *Zena-Lissan* Vol XXVII No 1. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማተሚያ፡፡

Abbink, Jhon. (1998). An Historical-anthropological approach to Islam in Ethiopia: Issues of identity and politics**;** *Journal of African cultural studies,* Volume11.

Abdullah, T. (2012). "Co-existence and Harmony in a pluralistic world: Gulen movement as wording model," paper presented at establishing and sustaining the culture of co-existence and mutual understanding conference of Ethiopian Federal Affairs. /Unpublished/.

Bascom,William R. (1965). Four functions of Folklore. Alan Dundes.(ed). *The Study of Folklore.Engle Wood Cliffs*: N.J Prentice.298-305.

Braukamper, U. (1992). Religious Syncretism in Southern Ethiopia, *Journal of Religion in Africa,* Vol.22, No.3.

Dorson, Richard.M. (1972). " Introduction: Concepts of Folklore and Folk life studies" in Richard. Dorson,*(ed.). Folklore and Folk life: An Introduction.* Chicago: University Chicago Press.

Dundes, Alan. (2004)."Foklorstics in the Twenty First *Century". Joumal of American Folklore. Vol.* 118 No. 470.

Murphy, A. (1997). "Toleration, and Liberal Tradition," *Journal of Polity,* vol. 29, No. 4.

Newman, J.(1978)."Idea of Religious Tolerance".*Journal of American Philosophy*,Vol.15, No.3.

Rukya H. (2018). A Step Further in Tolerance. *Global Journal of Arch & Anthropol*. Vol 4 No 1.

UNESCO. (1995). Declaration of principles on Tolerance proclaimed and signed by the Member States of UNESCO, Paris. /Unpublished/.

Tony Karbo. (July 2013). Religion and social cohesion in Ethiopia. *International Journal of Peace and Development Studies.* http://www.academicjournals.org/IJPDS